ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

ጥር 2003 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 26

# በከተማ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ልማት ስትራቴጂ ለድህነት ቅነሳ፣ የሥራ እድል ለመፍጠርና ለንግድ ሥራ መስፋፋት ያደረገው አስተዋጽኦ

## *በአራት ከተሞች የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ውጤት*

*የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡*

*የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡*

*በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡*

*በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡*

*በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡*

### *መግቢያ*

የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች መስፋፋት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በሰፊው ግንዛቤ አግኝቷል፡፡ ለሥራ እድል መስፋፋትና ለፈጠራ ችሎታ መዳበር የዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ በመልማት ላይ ባሉና በኢኮኖሚ በለሙ አገሮች ውስጥ የታወቀ ነው፡፡ እ.አ.አ. በ2004 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ተቋማት ድርሻ በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሥራ እድል ውስጥ በአሜሪካ 6.2%፣ በቻይና 22.3%፣ በሕንድ 80%፣ በጃፓን 67%፣ እና በአውሮፓ ሕብረት አገሮች 70% ይደርሳል፡፡ በይበልጥም ጠቀሜታው ጎልቶ የሚታየው በአውሮፓ ሕብረት አገሮች ሲሆን እ.አ.አ. በ2005 የተገኘ ማስረጃ እንደሚያመለክተው በነዚህ አገራት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ድርጅቶች ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ 99% ሲወክሉ ከ65 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ሰዎች ደግሞ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

አሁን በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ የእስያ ኢኮኖሚዎች በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ከአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ዕድገት ዋና ተጠቃሚ ነበሩ፡፡ የአገራቱ መንግስታት አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማታቸውን ለማፋጠንና ወደ ዓለምአቀፍ ገበያ ዘልቆ ለመግባት የተከተሉት የስትራቴጂ አቅጣጫ በውጭ ንግድና የመካከለኛ መጠን ባላቸው ኢንዱስትሪና ኢኮኖሚ ተቋማት ላይ ያተኮረ እንደነበረ ታውቋል፡፡ እነዚህ ተቋማት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ በማድረግ በማደግ ላይ የነበረውን ዓለምአቀፍ ገበያ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ስልጠና በመስጠት ግባቸውን ሊያሳኩ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም በተቋማት መካከል ተደጋጋፊና በትብብር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፍጠር፣ መረጃዎችንና የቴክኖሎጂ ዕቃዎችን መለዋወጥ፣ በጥናትና ምርምር፣ እና ስለቴክኖሎጂ ምንጮች መረጃ በማቅረብና አብሮ የመሥራት ባሕል እንዲዳብር በማድረግ መንግስታት ያደረጉዋቸው ጥረቶች ለውጤቱ መሳካት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መንግስት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪና የኢኮኖሚ ተቋማት ልማት በቂ ትኩረት አልሰጠም ነበር፡፡ ነገር ግን በከተሞች ተንሰራፍቶ የሚታየው ድህነትና ከፍተኛ ስራ አጥነት ወደዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ ፊቱን እንዲያዞር አድርጎታል፡፡ በተለይም መንግስት በቀየሠው “*በፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ*” አማካይነት የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን መስፋፋት ለመደገፍ ወስኗል፡፡ ከዚሁ የአምስት ዓመት ዕቅድ ጋር ተያይዞ በከተሞች አካባቢ የሥራ እድል ለመፍጠር እና ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ብድር የሚሰጡ የገንዘብ ድርጅቶችን ለማበረታታት መንግስት ባዘጋጀው የከተሞች መልካም አስተዳደርና መርሐግብር ዓቢይ ትኩረት

ተሰጥቷል። ይህም መርሐግብር የሚከተሉት አላማዎች አሉት፡-

- ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችንና የኢኮኖሚ ተቋማትን በማስፋፋት የከተማ ሥራ አጥነትንና ድህነትን መቀነስ፤
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችንና የንግድ ተቋማትን እድገት ለማፋጠን ከመካከለኛና ትላልቅ ተቋማት ጋር ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ፤
- የንግድ ተቋማቱ የሚያድጉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለወደፊት የአገሪቱን ኢንዱስትሪ ልማት ጠንካራ መሠረት መጣል፤
- በገጠርና በከተሞች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ትስስር ማጠናከር፤ ናቸው፡፡

መንግስት ለጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ተቋማት መስፋፋት ከፍተኛ ግቦችን አስቀምጧል:: በዚሁ መሰረት እ.አ.አ. በ2006/07 -09 ባለው ጊዜ በ825 ከተሞች 1.5 ሚሊዮን የሥራ እድሎች ለመፍጠር፣ ከዚህ ውስጥ ግማሹ ተጠቃሚዎች ሴቶች እንዲሆኑ ተብሎ ታቅዷል፡፡ በጠቅላላ ለሥራው መንግስት 6.2 ቢሊዮን ብር መዋዕለንዋይ ለማፍሰስና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማልማት በከተሞች ውስጥ 4900 ሄክታር መሬት የሚመድብ መሆኑ በመርሐግብሩ ተገልጿል፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት መንግስት ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና የኢኮኖሚ ተቋማት ትኩረት ሰጥቶ በከፍተኛ ደረጃ የተንቀሳቀሰ ቢሆንም እነዚህ ተቋማት የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ፣ ድህነትን በመቀነስና ቀጣይነት ያለው የንግድ ዕድገት ለማረጋገጥ ያደረጉት አስተዋፅኦ በውል አልታወቀም፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላት የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የተገኙትን ውጤቶችና ቀጣይነታቸውንም በተመለከተ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ኢኮኖሚ ተቋማት በፍጥነትና ቀጣይነት ባለው መንገድ እንዲያድጉ የሚያግዙ የፖሊሲ ግብአቶችን ማቅረብና የዳበረ የጥቃቅንና አነስተኛ የኢኮኖሚ ተቋማት ለአገሪቱ ሁለንተናዊ ልማት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ማጎልበት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን ዐበይት ጥያቄዎች በማንሳት ምላሽ ለመስጠት ሙከራ አድርጓል፡-

- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የኢኮኖሚ ተቋማት ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊነት ምን ይመስላል? የአፈጻጸሙ ዋና ዋና ተግባራት ምን ምን ናቸው?
- የልማት ስትራቴጂው የሥራ ዕድገት በመፍጠርና በድህነት ቅነሳ ረገድ ምን ውጤት አስገኝቷል?
- በክፍለ ኢኮኖሚው ተሳታፊዎች ሕይወት ላይ ምን ተጨባጭ ለውጥ አምጥቷል? በገቢስ በኩል ምን መሻሻሎች ይታያሉ?
- በድርጅቶቹ አማካይነት የተፈጠረው የሥራ ዕድል በስፋትና በጥልቀት ምን ይመስላል?
- በነዚህ የኢኮኖሚ ተቋማት አማካይነት በንግድ ልማትና ዕድገት ረገድ የተገኘው ውጤት በዘላቂነት የመቀጠሉ ሁኔታ እንዴት ይገመገማል?
- ተሳታፊዎቹ እና ባለቤቶቹ ያጋጠሟቸው ችግሮችና ፈተናዎች ምን ምን ነበሩ? ምንስ የመፍትሔ እርምጃዎች ተወስደዋል?

## የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ በአራት የክልል ከተሞች ማለትም አዳማ፣ ሐዋሳ፣ ባሕር ዳርና፤ መቀሌ የተካሄደ ሲሆን እነዚህ ከተሞች የተመረጡትም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢኮኖሚ ተቋማት ክምችት ያለባቸው መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በ2002 ዓ.ም ነበር፡፡ መረጃ የተሰበሰበው ለናሙና በተመረጡ በእያንዳንዱ ከተማ 50 ተቋማትና 200 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ባለቤቶችንና ተሳታፊዎችን በናሙና በመውሰድ ነው:: በተጨማሪም በኢኮኖሚ ተቋማቱ መስፋፋትና ማደግ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የስራ ኃላፊዎችንና ባለድርሻዎችን፣ ማለትም የከተሞች አስተዳደርና አመራር ኃላፊዎችን፣ የቢሮና የሴክተር መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችንና የጥቃቅንና አነስተኛ የገንዘብ ቁጠባ ተቋማት ኃላፊዎችን፣ እንዲሁም በተለያየ ደረጃ ያሉ ሠራተኞችን አሳትፏል፡፡ ከተለያዩ ተሳታፊዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በስታቲስቲካዊና በገላጭ የጥናት ዘዴ ከተተነተኑ በኋላ ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶች

### የተመሠረቱት ተቋማት ብዛትና የተፈጠረው የሥራ ዕድል መጠን

እ.አ.አ እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በአራት ትላልቅ ክልሎች ማለትም በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በድምሩ 71,568 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ተቋማት ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህም ለ395,806 ወገኖች የሥራ ዕድሎችን ፈጥረዋል፡፡

### የብድር አሰጣጥ

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ኢኮኖሚ ውስጥ ብድር ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ተቋማት መመሥረትና ማደግ ወሳኝነት አለው:: በአመዛኙ ብድር የሚሰጠው በክልል መንግሥታት ሥር ባሉ የጥቃቅንና አነስተኛ የብድር ተቋማት ነው፡፡ እ.አ.አ. በ2002 ዓ.ም ብቻ እነዚህ ተቋማት ከ423 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር ሰጥተዋል:: 77,856 ተጠቃሚዎች ተመዝግበዋል:: ሆኖም በብድር ፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ልዩነት ይታያል፡፡ በሁሉም ክልሎች የብድር ፍላጎትና አቅርቦት ባለመመጣጡኑ ምክንያት በብድር ዕጦት ሳቢያ ብዙ የንግድ ተቋማትና አዳዲስ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ያልገቡበት ሁኔታ አለ፡፡

### የመገበያያና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት

በቂ የማምረቻና የመገበያያ ቦታ ማግኘት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት ማደግ ወሳኝነት አለው፡፡ በዚህ ረገድ ክልሎች ከፍተኛ ውጤቶችን አስመዝግበዋል:: ለምሳሌ ትግራይን ሳይጨምር እ.አ.አ. በ2009 ዓ.ም በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች 343,817 ተጠቃሚዎች እንደነበሩ ታውቋል:: እ.አ.አ. በ2008 ዓ.ም ትግራይ ውስጥ ማምረቻና መገበያያ ማዕከሎችን በ38 ከተሞች ለማቋቋም 52 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኗል:: በደቡብ የክልሉ መንግሥት የተቋማት ስብስብን ለማስፋፋት 40% ወጪውን ሲሸፍን ከተሞች ደግሞ 60% ወጪውን እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

### የሥልጠና ድጋፍን በተመለከተ

በሁሉም የጥናቱ ከተሞች ሁለት ዓይነት ስልጠና ይሰጣል፤ እነሱም የቴክኒክና የንግድ ሥራ ሙያ ናቸው:: በዋነኛነት ስልጠናውን የሚሰጡት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ናቸው:: በተጨማሪም የህብረተሰብ ማሰልጠኛ ማዕከላትም በማሠልጠን ሥራው ይሳተፋሉ:: እ.አ.አ. በ2009 በተገኘው መረጃ መሠረት በአራቱ ክልሎች ለ324,141 ሰዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

### የገበያ ትሥሥር

የገበያ ትሥሥር መኖር ለጥቃቅን ምርቶችና አገልግሎቶች፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ተቋማት የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ ነው:: የተቋማቱ ብዙው የገበያ ትስስር የተመሰረተው ከመንግስት ድርጅቶች ጋር ነው:: ለምሳሌ የግንባታ ተቋማት ከጋራ መኖሪያ ቤቶች (ከኮንዶሚኒየም) ግንባታ ሥራ ጋር ይቆራኛሉ:: የምግብና መጠጥ ተቋማት ደግሞ ከዩኒቨርስቲዎች እና ወህኒ ቤቶች አስተዳደሮች ምግብ የማቅረብ ሥራ ጋር እንደተሳሰሩ ታውቋል፡፡ የክልል መንግስታት ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የጨረታ ውድድሮችን ሳያሟሉ እንዲሳተፉ ያደረጉበት ሁኔታም አለ:: የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በአራቱ ክልሎች 95,931 ተቋማት የገበያ ትሥሥር ተጠቃሚ ሆነዋል:: ይህም በገንዘብ ሲገመት 838 ሚሊዮን ብር ይሆናል፡፡

### የተሳታፊዎች ገቢ መጨመር እና የስራ አጥነት መቀነስ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እና ተቋማት መስፋፋትና መጠናከር የተሳታፊዎችን ገቢ ጨምሯል፡፡ የገቢ መጨመር ተጠቃሚዎች ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ አስተዋጽኦ አድርጓል፤ ይህም ለድህነት ቅነሳ ረድቷል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እና ተቋማት መስፋፋት የሥራ አጥነትን በከተሞች ቀንሷል:: በተለይም በወጣቱ አካባቢ በይበልጥ ደግሞ በአንዳንድ ክልሎች ሴቶች ተጠቃሚ የሆኑበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ለምሳሌ፤ በትግራይ ክልል ሥራ ካገኙት ውስጥ 54% ሴቶች ሲሆኑ በአማራ ክልል ደግሞ 57% የሚሆኑት ተጠቃሚዎች ሴቶች ናቸው፡፡ በአራቱ የጥናቱ ከተሞች የሴት ተጠቃሚዎች ቁጥር በአማካይ 39% መሆኑ ታውቋል፡፡

### የመነሻ ካፒታል ዕድገት

የብዙዎቹ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ተቋማት የመነሻ ካፒታል ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል:: ለምላሌ በመቀሌ፣ በባሕር ዳርና በአዳማ የተሰማሩት ተቋማት የመነሻ ካፒታላቸው መጠን ከስድስት ጊዜ በላይ ዕድገት አሳይቷል:: በተለይም በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ተቋማት ያስመዘገቡት የካፒታል ዕድገት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### የሳምንታዊ ሽያጭ ሁኔታ

የሁሉም ዓይነት ተቋማት ሳምንታዊ ሽያጭ በአማካይ 6,000 ብር ደርሷል:: አንዳንድ መረጃ ዎች እንደሚጠቁሙት በአዳማ ያለው ሳምንታዊ የሽያጭ መጠን እስከ 10,000 ብር እንደሚደርስ

ሲገመት፣ በምግብና ምግብ-ነክ እንዲሁም በግንባታ ሥራዎች የተሰማሩ ተቋማት ከፍተኛ መጠን የሳምንት ሽያጭ አስመዝግበዋል::

### ለንግድ ሥራ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያሉት ነባራዊ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎች ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ድርጅቶችና ንግድ ተቋማት በአንዳንድ በኩል አመቺ ሆነው ተገኝተዋል:: ለምሳሌ አባላት ትርፋቸውን በአክሲዮን ድርሻ መልክ እስካልወሰዱ ድረስ የመንግስት ታክስ እንዳይከፍሉ አለመገደዳቸው በዋነኛነት ይጠቀሳል:: በአንዳንድ ክልሎች፣ ለምሳሌ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ፣ ተቋማቱ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ከግብር ክፍያ ነፃ ናቸው:: በተጨማሪም ፈቃድ ለማውጣት፣ ለመመዝገብ፣ ለግብር አስተዳደር፣ የሠራተኛ ሕግ፣ የንግድ ቁጥጥር፣ የመሳሰሉትን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና ሕጐች ለእነዚህ ተ ማት የሥራ እንቅስቃሴዎች እንቅፋት እንዳልሆኑ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል:: በሌላ በኩል ደግሞ የመሥሪያና የመገበያያ ቦታ ለማግኘት ያለው ችግር፣ የገበያ እጥረት፣ በቂ ብድር ያለመኖርና የመብራት ኃይል በየጊዜው መቋረጥ እንደ ዋና ችግር በተቋማቱ ተጠቁመዋል::

### የገበያና የንግድ ትስስር ውስንነት

በጥናቱ በተገኘው መረጃ መሠረት አብዛኞቹ አነስተኛ የኢኮኖሚ ተቋማት ማለትም 60% የሚሆኑት ከሌሎች አቻ ድርጅቶች ጋር የገበያም ሆነ የምርት ትስስር እንደሌላቸው ገልፀዋል:: የትብብር ሥርዓትና አሠራር አለመዘርጋቱና በተ ቋማቱ መካከል በሥራ ጉዳይ መተማመን አለመኖሩ በዋናነት እንደ ምክንያት ተነስተዋል::

### የፖሊሲ መወያያ ሃሳቦች

- የግል የብድርና የቁጠባ ድርጅቶች ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ሥራ ቋማት ብድር ለመስጠት እንዲችሉ ሁኔታ ዎችን ማመቻቸት፣
- የገበያ እጥረትን ወይም አነስተኛነትን እና የጥሬ ዕቃ ግብዓቶች አቅርቦት ችግሮችን ተቋማቱ መቋቋም እንዲችሉና በነፃ ገበያ ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ስትራቴጂ በማውጣት መንቀሳቀስ፣
- የሚሰጡትን ድጋፎችና አገልግሎቶች ጠንካራና ደካማ ጐኖች መፈተሽና የተሻለ ውጤት የሚያስገኙበትን መንገድ መቀየስ፣
- አሁን የሚታየውን ውስን የገበያና የምርት ትስስር እና በከተሞች ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በገጠሩ ካለው የእርሻ ኢኮኖሚ ጋር የሚያሳየው ዝቅተኛ ቁርኝት ለማሻሻልና ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር አስፈላጊ ዕርምጃዎችን መውሰድ፣
- በመንግሥት ድጋፍ ለተቋቋሙት አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና የኢኮኖሚ ተቋማት ብቻ ብዙ ድጋፍ የማድረግ አሰራር እንደገና እንዲገመገም እና ከዚህ አልፎም በራሳቸው ተነሳሽነት የሚቋቋሙትንና አሁን በሥራ ላይ ያሉትን ተቋማት ለመርዳትና ለማበረታታት መርሐግብር አወጥቶ መንቀሳቀስ፣
- በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች እና በአገሪቱ ትላልቅ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ቁርኝት እና ውህደት ማጠናከር አስፈላጊነት::

**ተገኝ ገብረ-እግዚያብሔር (ፕ/ር)**
**ምህረት አየነው (ዶ/ር)**

**ምንጭ**:- Tegegne Gebre-Egziabher and Meheret Ayenew. 2010. *Micro- and Small Enterprises as Vehicles for Poverty Reduction, Employment Creation and Business Development: The Ethiopian Experience* . FSS Research Report No. 6. Addis Ababa: Forum for Social Studies (FSS).

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በሊጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲያኑ ሲሆን በምንም ሁኔታ የሊጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም::

አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
❄ ስልክ 011-629 78 88/91 ❄ ፋክስ 011-629 78 89
❄ ኢሜይል: fss@ethionet.et ❄ ድረ-ገፅ www.fssethiopia.org.et